ኢ ዴ አ ፓ - መ ድ ኅ ን
UEDP - MEDHIN
Head Office ☐ Branch Office ☐ Support Group ☐

ቀን 13/8/1999 ዓ.ም
Date
ቁጥር ኢ.መ 047/99
Ref.

# ሰሞኑን በሶማሌ ክልል የተፈፀመውን የሽብር ድርጊት በተመለከተ
## ከኢዴአፓ-መድህን የተሠጠ መግለጫ

በማንኛውም ሁኔታ የፖለቲካ አመለካከትን በኃይል ለማስፈፀም የሚደረግ ጥረትን፣ በተለይም ደግሞ በሲቪል የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚፈፀምን የአሸባሪነት ድርጊት ኢዴአፓ-መድህን አጥብቆ ይቃወማል። ሚያዚያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም በአገራችን የሶማሌ ክልል በነዳጅ ፍለጋ ስራ የተሠማሩ 65 ሲቪል ኢትጵያውያንና ዘጠኝ የቻይና ዜጐች ላይ የተፈፀመውን እጅግ ዘግናኝ የሆነ የጭፍጨፋ ድርጊት ፓርቲያችን ኢዴአፓ-መድህን በጥብቅ ያወግዛል። እንዲህ አይነቱ አሰቃቂ ድርጊት በአገራችን የሰላምና የልማት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትልና ከአጠቃላዩ ብሔራዊ ደህንነታችን ጋር በእጅጉ የተቆራኘ አደጋ በመሆኑ ሕዝብና መንግሥት በጋራ ሊታገሉት የሚገባ አሳሳቢ ድርጊት ነው ብለን እናምናለን። አለም አቀፉ ህብረተሰብም ይህንን ዘግናኝ የሽብር ድርጊት በጥብቅ ሊያወግዘው ይገባል እንላለን። መንግሥት ይህንን ድርጊት የፈፀሙ ኃይሎችን ለፍርድ ለማቅረብም ሆነ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ለሚወስደው አስፈላጊ እርምጃ ሁሉ ፓርቲያችን ኢዴአፓ-መድህን የበኩሉን ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን እየገለፀ፣ በዚህ የጭፍጨፋ ድርጊት ቤተሰቦቻቸውን ላጡ ወገኖች ሁሉ መፅናናትን ይመኛል።

የኢዴአፓ-መድህን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
ሚያዚያ 18 1999 ዓ.ም
<u>አዲስ አበባ</u>

UEDP-MEDHIN COUNCIL HEAD OFFICE

Head Office Addis Ababa ☎ 50 87 27 50 87 28 ✆ 50 87 30 ✉ 101458 E-mail:addisedepa@hotmail.com
Our Account No. Addis Ababa, Bank of Abyssinia Filwuha Branch A/C 145
Branch Office or Support Group in ______ Tel: ______ Fax: ______ P.O.Box: ______
E-mail: ______